# የዜጎች መድረክ

ኢዜማ

ቅፅ 1 ቁጥር 20 ህዳር 18 ቀን 2012 ዓ.ም
በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

## ግብር እና ማኅበራዊ ፍትሐዊነት



# ኢዜማ፣ የኢህአዴግ ድርጅቶች ስለሚፈጥሩት ውህድ ፓርቲ

የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ተዋህደው አንድ አገራዊ ፓርቲ ለመመሥረት መወሰናቸው የአገራችንን ፓለቲካ ያዘምናል ብሎ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ ፓርቲ (ኢዜማ) ተስፋ ያደርጋል። በዚህም ምክንያት ኢዜማ በኢህአዴግ ውስጥ ለሚገኙ ለውጥ ፈላጊና አገር ወዳድ ወገኖቻችን እንኳን ደስ ያላችሁ ይላል፤ ለሀገርና ሕዝብ የሚጠቅም እርምጃ የወሰዳችሁ በመሆኑ በመካከላችን ያሉ ልዩነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ደስታችሁ ደስታችን ነው።

በጉልበት መግዛት በጭራሽ የማይታሰብበት አገር መገንባት ይኖርብናል። ከመፎካከር ይልቅ ለመጠፋፋት የተደራጁ ፓርቲዎች የማይኖሩበት የፓለቲካ ምህዳር መፍጠር ይኖርብናል። በምርጫ ተወዳድሮ ማሸነፍ የፓለቲካ ፓርቲዎች ሁሉ የሚመኙት ውጤት ቢሆንም በምርጫ መሸነፍ የፓርቲውንም ሆነ የመሪዎቹ ህልውና አደጋ ውስጥ የማይጥልበት አገር እንዲኖረን እንሻለን። በሕዝብ ነፃ፣ ፍትህዊና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ማሸነፍንም በተመለከተ አንድ ፓርቲ በአንድ ምርጫ ስላሸነፈ ብቻ ያሻቸው መፈፀም የማይችልበት፤ ተሸናፊዎች ተጠናክረው ቢመጡ በሚቀጥለው ምርጫ የማሸነፍ እድላቸው ዝግ ያልሆነባት አገር ማየት እንሻለን። የተሸናፊው ፓርቲ መሪ የአሸናፊውን ፓርቲ መሪ "እንኳን ደስ ያለህ" የሚልበት አገር ውስጥ መኖር እንመኛለን። አዲሱ ውህድ ፓርቲ እነዚህን ትልሞቻችንን ተግባራዊ ለማድረግ በምናደርገው ትግል አጋዥ ኃይል ይሆነናል ብለን እናምናለን።

ውህዱ ፓርቲ የኢትዮጵያን ፓለቲካ ለማዘመን ትልቅ አስተዋጽዖ ሊያደርግ ይችላል። የኢትዮጵያ ፓለቲካ፣ የዘር ሀረጋቸውን ቆጥረው የተሰባሰቡ ቡድኖች ድርሻቸውን ለማብዛት የሚያደርጉት "የይገባኛል" ፉክክር ሳይሆን "ኢትዮጵያን የሚበጃት የፓለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ፓሊሲ የትኛው ነው?" በሚል በፖሊሲ አማራጮች ላይ የሚያደርጉት ክርክር እንዲሆን መታገል ከውህዱ ፓርቲ ቀዳሚ ተግባራት አንዱ መሆን ይኖርበታል ብሎ ኢዜማ ያምናል።

"በአብዮታዊ ዲሞክራሲ" ንድፈሀሳብ ተኮትኮ ካደገ ድርጅት የሀገርን ብልጽግናና ክብር ዓላማው ያደረገ ውህድ ፓርቲ መፍጠር ምን ያህል ፈታኝ እንደሆነ እንገነዘባለን። ኢህአዴግ ይህንን ፈተና በአሸናፊነት ከተወጣ ከአምባገነን ፓርቲነት ወደ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲነት በሰላማዊ መንገድ የተሸጋገረ ፓርቲ ያደርገዋል። ይህን ለማድረግ ደግሞ ዕድሉ አለው።

ከፊታችሁ ተደቅነው የነበሩ ችግሮች ተጋፍጣችሁ እዚህ ድረስ ደርሳችኋል፤ ወደፊትም ብዙ ጋሬጣዎች ሊገጥሟችሁ ይችላሉ፤ ሆኖም የጀመራችሁት መንገድ ለአገራችን ኢትዮጵያ እና ሕዝቧ የሚጠቅም ነውና ድጋፋችንን እንሰጣችኋለን። ውህዱን ፓርቲ ለመመሥረት በመቃረባችሁ በድጋሚ እንኳን ደስ ያላችሁ እንላለን።

# የአዲስ አበባ ከተማ 133ኛ ዓመት ምስረታን በማስመልከት የፓናል ውይይት ይካሄዳል

ሕዳር 18 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)




የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የአዲስ አበባ ከተማ የተመሰረተችበትን ፻፴፫ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ ከታዋቂ የታሪክ ተመራማሪዎችና በዘርፉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የፓናል ውይይት ለማድረግ ዝግጅቱን አጠናቋል።

ቀን ህዳር 19 ቀን 2012 ዓ.ም
በጣይቱ ሆቴል
ከቀኑ 7፡00 ጀምሮ

+ 251 953132820 + 251 118592950

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) የፊታችን አርብ ሕዳር 19 ቀን 2012 ዓ.ም በጣይቱ ሆቴል አዲስ አበባ ከተማ የተመሰረተችበትን 133ኛ ዓመት እንደሚያከብር የኢዜማ ም/ ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አስቻለው ደምስ ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

ኢዜማ በጣይቱ ሆቴል በሚያካሄደው ዝግጅት ላይ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች፣ የሚዲያ አካላትና ምሁራን የሚገኙ ይሆናል፡፡ በእለቱ ታዋቂ ምሁራን የአዲስ አበባ ከተማ አመሰራረት በሚመለከት የፓናል ውይይት እንደሚያደርጉ ከወጣው መርሃግብር ለመረዳት ተችሏል፡፡ ፕሮግራሙ ከቀኑ 7፡00 እንደሚጀምር ለዜጎች መድረክ የደረሰው መረጃ ያስረዳል፡፡


## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema


የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

ህዳር 18 ቀን 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ግብር እና ማኅበራዊ ፍትሐዊነት

እንደ ኢትዮጵያ ባሉና “ታዳጊ” ተብለው በሚጠሩ አገራት ግብር ዋና የገቢ ምንጭ አይደለም። ሙሉ በሙሉ ወጪያቸውን ከግብር እና ከውጪ ንግድ ሸፍነው ከዚያም አልፈው ከፍ ያለ ትርፍ ገንዘብ የሚተርፋቸው አገራት “ያደጉ” ተብለው ይጠራሉ። በአንጻሩ አገራችን ዘመናዊ የሚባለው የአስተዳደር፣ የምጣኔ ሃብትና የፖለቲካ ሥርዓት ከተቀበለችበት ጊዜ አንስቶ የራሷን ወጪ በእራሷ ምርትና ምርታማነት ገቢ ብቻ ሸፍና አታውቅም። እንደ ሌሎች ታዳጊ አገራት ሁሉ ኢትዮጵያም ተጨማሪ ወጪዋን ለመሸፈን እርዳታ እና ብድር ስትቀበል ኖራለች።

ለዚህ ሁኔታ በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም ዋናው ምክንያት አገራችን ቴክኖሎጂ ተቀባይ አገር መሆኗ ነው። ኢትዮጵያ የበርካታ ፈጠራዎች ባለቤት አገር ብትሆንም በተለይ ከ18ኛውና 19ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የአውሮፓ አገራት የደረሱበትን የቴክኖሎጂ እድገት ለመድረስ የሚያስችላት የእውቀትና ብረታ ብረት የመሳሰሉ የማዕድን ሃብት አቅም አልነበራትም። በአጠቃላይ ግሎባል ሳውዝ በመባል የሚታወቁትና በአብዛኛው በቅኝ ግዛትና በባርነት ሥርዓት ሲማቅቁ የነበሩ አገራትም ችግግር ተመሳሳይ ነው። ስለዚህ ለአገራችን እድገት የሚያስፈልጉና እንደ መንገድ እና ኤሌክትሪክ ኃይል ካሉ መሰረታዊ ልማት አውታሮች ጀምሮ እስከ ኮምፒዩተርና ስልክ ድረስ ያሉ ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮች በሙሉ ከውጭ የሚገቡ በመሆናቸው ከአገራችን ምርት በሚሰበሰብ ገቢ ሊሸፈን አይችልም።

አንድ መታረም ያለበትና የተለመደ የእይታ ችግር የግብር ገቢያችንን ወይም ግብር አለመከፈልን እንደ ድኅነት ምንጫችንና ለአገራችን ድኅነት ዋና ተጠያቂነት አድርጎ የማቅረብ ነው። የአገራችን የግብር ገቢ መጠን የድኅነታችን ምክንያት ሳይሆን የድኅነታችን አንዱ መገለጫ ነው፤ ምክንያቱም ግብር የሚሰበሰበው ከምርት ነው። ካልተመረተ ወይም ግልጋሎት ካልተሰጠ ገቢ የለም፣ ገቢ ከሌለ ግብር አይሰበሰብም። ኢትዮጵያ አገር ከሆነችበት ጊዜ አንስቶ ግብር ስትሰበስብ ቆይታለች፣ ኖራለች። ግብር መሰብሰብና ግብር ማስገበር መቻል በየትኛውም አገር የመንግሥትነትና የአገርነት ሕልውናና ጥንካሬ መለኪያ ሆኖ ቆይቷል፣ አሁንም ነው። ከድኅነት ቀጥሎ በጣም መሰረታዊ (Basic) የሆነው የመንግሥት ሚና ጠንካራና ተዓማኒ የግብር ሥርዓት ዘርግቶ ከግብር ውጪ የሚንቀሳቀሰውን ኃይል ጉልበትና ቁጥር መቀነስ ነው። ይህ ሥርዓት በጣም ልልና ለማጭበርበር ቀላል ሆኖ የአገሪቱ ምርትና ምርታማነት እየጨመረ በአንጻሩ የግብር ገቢው የማይጨምር ከሆነ መታረም ያለበት የግብር ሥርዓቱ እንጂ ግብር ከፋዩ ሕዝብ አይደለም። ይህ ሳይሆን ከቀረ ግን ቤትን ክፍት አሳድሮ ሰውን ሌባ እንደማለት ነው የሚሆነው ነገሩ።

## 1) የግብር ሥርዓት ተዓማኒነት

ከላይ መግቢያችን ላይ የጠቀስነው የእይታ ችግር ውጤት አንዱ የግብርን ገቢ መጠን እንደ መንግሥት ግዴታ ሳይሆን እንደ መንግሥት ብሎም እንደ አንድ ፓርቲ ድል አድርጎ የማየት ነው። ዛሬ አንድ ኢትዮጵያዊ ግብር ከፋይ የሚከፍለው ግብር ምን ላይ እንደሚውልና የሚውልበትን ዓላማ አያውቅም፣ አልተስማማበትም፣ አልተነገረውም እንዲሁም አይጠይቅም። የሚከፍለው ግብር ምን ላይ እንደሚውል የመጠየቅ ሰብዓዊ መብት እንዳለውም አያውቅም።

ግብርን ከማኅበራዊ ፍትሕ ጋር የሚያስተሳስረው የመጀመሪያው ነጥብም ይህ ነው። ግብር መክፈል መንግሥትና ሕዝብ የሚገናኙበት ቁልፍ የእምነት መስመር ነው። ግብር ማለት ግብር ከፋዩ ለሚያገኘውና የአንድ መንግሥት ዋና ተግባራት ለሆኑት የሕይወት፣ የንብረትና የአገር ደኅንነት፣ የአስተዳደር፣ የመሰረታዊ ልማትና የፍትሕ ሥርዓት ወጪ የሚያዋጣው ገንዘብ ነው። ግብር ከፋዩ ከነዚህ የመንግሥት ተግባራት በአንዱ እምነት ወይም የባለቤትነት ስሜቱን ሲያጣ በግብር ሥርዓቱ ላይ ተስፋ ይቆርጣል። ከዚህ በኋላ የሚከፍለው ግብር በእምነት ሳይሆን በባሰ ቅጣት ፍራቻ ነው።

ባለፉት 28 ዓመታት በተዘረጋውና በሁሉም አቅጣጫ ኢፍትሐዊ የሆነ ሥርዓት ሳቢያ ዛሬ በሕዝባችን ላይ የሰፈነው የእምነት እጦት የግብር ሥርዓቱን ተዓማኒነት ፍጹም አሳጥቶታል። በምጣኔ ሃብት ባለሞያዎች እንደሚታወቀው በአንድ አገር ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ውስጥ “እምነት” በገንዘብ የሚተመን ዋጋ አላት ። ከአንድ እስከ አስር በተቀመጠው የአገራት የእምነት መጠን መለኪያ ለምሳሌ አገራችንን ጨምሮ ሁሉም የአፍሪካ አገራት የሰፈነው የእምነት ደረጃ ከዜሮ እና አንድ የማያልፍ ነው። ይህ በእለት ተእለት ኑሯችን በገንዘብ ሲመነዘር ለምሳሌ አንድን እቃ ለመገብየት የበርካታ ሰዎችን ምክር በመጠየቅ፣ ቤት ለማከራየት የስድስት ወርና ከዛም በላይ ቅድሚያ ክፍያና ተቀማጭ መጠየቅ፣ ለአቅራቢ የሚከፈልን ገንዘብ ያለ ምክንያት በማዘግየት፣ በቀጥታ የእራስን ጉዳይ በእራስ ከማስፈጸም ይልቅ በደላሎችና በጉዳይ ፈጻሚዎች መስራትና በነሱ መበራከት፣ በተለይ ደግሞ የዚህ አሰራር ውጤት የሆነው ሙሰኝነት በመስፋፋትና በመሳሰሉት በርካታ ሁኔታዎች ይገለጻል። እነዚህን የመሳሰሉ የእምነት ማጣት ውጤቶች ኢኮኖሚውን በአጠቃላይ በማጓጓተትና ዋጋ በማስወደድ ያሽመደምዳሉ። የኢኮኖሚው መሽመድመድ ደግሞ በተራው የግብር ገቢውን መጠን ያሳንሳል።

ኢዜማ ይህንን እርስ በእርስ የተሳሰረ ውስብስብ የአሉታዊ ተጽዕኖ ሰንሰለት እስከወዲያኛው ለመስበር አገራችን ወደ ዲሞክራሲ የምታደርገውን ጉዞ አጽንታ መቀጠል እንዳለባት ቢያምንም ጉዞውን ለማሳካትም ሆነ የአገራችንን የገንዘብና የሰው ኃይል አቅም ለማገናዘብ የሚረዱና በአጭር ጊዜ ሊከናወኑ የሚችሉ ተግባራት ዝርዝር አስቀምጧል። በዚህ ረገድ የመጀመሪያው ተቀዳሚ ተግባራችን የሚሆነው ከፍተኛ የግብር ግልጽነት ደረጃ ማስረጽ ነው።

ሌሎች የአገራችን ተቋማት በበቂ ደረጃ ባልተጠናከሩበት ሁኔታም ቢሆን የግብር ግልጽነትን ማስፈን በመንግሥትና በሕዝብ መካከል የተበጠሰውን የእምነት ግንኙነት ለማረቅና ለማያያዝ ከፍተኛ አስተዋጾ እንደሚኖረው እናምናለን። ይህንን የግብር ግልጽነት ለማስፈን ደግሞ ሰፊ የግብር መረጃ መረብ መዘርጋት በአፋጣኝ መስራት ያስፈልጋል። ስለዚህ እንደ ንግድ ፍቃድና ደረሰኝ ሁሉ በግብር ከፋዩና በግብር ተቀባዩ አካል ላይ ዓመታዊ የግብርን መጠን የማሳወቅ/ ይፋ የማድረግ ሕጋዊ ግዴታ መጣል ያስፈልጋል። ይህ አሰራር በሁሉም ያደጉ አገራት ያለ ሲሆን በአገራችንም መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች (መያድ) ላይ ቢያንስ በሕግ ደረጃ ያለ ነው። እያንዳንዱ ግብር ከፋይ ምን ያህል እና ለየትኛው አካል እንደከፈለ ይፋ የማድረግ ግዴታ መጣል ከሚያስገኛቸው ጥቅሞች መካከል:-

- መንግሥት ያን ያህል ወጪ ሳያወጣ በአገሪቱ ውስጥ ያለውን የግብር ከፋይ ብዛትና እርከኖች (ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ አነስተኛ) የሚያሳይ መረጃ ማሰባሰብ ይችላል፣ ይህም የግብር ሥርዓቱን በሁለገባዊ መንገድ ለማሻሻል እጅግ አስፈላጊ የሆነውንና የዘገየውን አገራዊ ጥናት ለማካሄድ ግብዓት ይሆናል።
- በአሁኑ ሰዓት በግለሰቦች ደረጃ የሚሰራውን የግምትና የልኬት ደረጃ የሚሰራውን አሰራር በማስቀረት ለሙሰኝነት ተጋላጭነቱን ይቀንሳል፡፡
- በግብር ከፋዩ አካባቢ ባለው ማኅበረሰብና ባለሙያዎች ወይም ተመሳሳይ ልምድ ባላቸው ሰዎች የግብር ከፋዩን ተቀባይነት ይጨምራል፡፡
- በተለይም ደግሞ በተመሳሳይ ዘርፍ በተሰማሩ ግብር ከፋዮች መካከል የውድድርና የመመዘዘን በር በመክፈት በአሁኑ ጊዜ በመንግሥት አካል ውስን አቅም ብቻ የሚሰራውንና ለበርካታ ችግሮች ተጋላጭ የሆነውን የግብር ክፍያ ግምትና ኦዲት ሥራና ወጪ ይቀንሳል፡፡

የግብር ክፍያ መጠንን ይፋ የማድረጉ ስራ የሚከናወነው በአንድ ቀን ስብሰባና የሚድያ ሽፋን ሳይሆን እንደ ንግድ ፍቃድ ሁሉ ዓመቱን ሙሉ ሕዝብ ሊያይና ሊገመግም በሚችልባቸው የድረ ገጽና ተመሳሳይ የማሳወቂያ መንገዶችን በመጠቀም ነው። (ተያያዥና የማይናቅ አስተዋጾ ለወጣቶች የሚፈጥረው የስራ እድል ነው።) ይህ ሕግ የሚመለከተው የግሉን ሴክተር ቢሆንም ግብር ሰብሳቢው በተመሳሳይ ሁኔታ በድረ ገጹ ላይ ከእያንዳንዱ የግል ንግድ ተቋማት የተሰበሰበውን ግብር የማሳወቅ ግዴታ ይኖርበታል። የግብር ክፍያ ደረሰኝ በአንድ የመንግሥት ሰራተኛ ማኅደር ውስጥ ቆልፎ የማስቀመጥ አሰራር መቅረት አለበት።

## 2) የግብር ሥርዓቱ ራዕይ

በመግቢያችን እንደጠቀስነው ታዳጊ አገራት ወጪያቸውን በግብር ገቢ መሸፈን ባይችሉም የእድገታቸውን አቅጣጫ እና አጠቃላይ የአገራቸውን ራዕይ በግብር ሥርዓታቸው ማንጸባረቅና መምራት ይችላሉ። ይህም ሁለተኛ ግብር እና ማኅበራዊ ፍትህ ተያያዥ የሚሆኑበት ሁለተኛው ነጥብ ነው።

ግልጽና የኢኮኖሚ አቅጣጫ ሥርዓት መቀየስ የሚችል የግብር ሥርዓት ዓላማ ግብር በከፋዩና በተቀባዩ መካከል የሚደረግ የእምነት ግብይት ለመሆኑ አንዱ ማሳያ ነው። ለምሳሌ ግብር ያለ አሳማኝ ምክንያት ወይንም ያለ ምንም ትንበያ (predictability) የሚዋዥቅ ከሆነ (ከዓመት ዓመት የሚጨምር) የግብር ሥርዓቱ ዓላማ በተገኘው ወቅታዊ አጋጣሚ መንግሥት ገቢውን ለማሳደግ ብቻ የሚጠቀምበት ነው ማለት ነው። በሌላ አገላለጽ መንግሥት የግል ዘርፉን እንደ ልማት አጋር ሳይሆን እንደ ገንዘብ ምንጭ ብሎም እንደ ጠላት የሚያሳይ የግብር ሥርዓት ነው ማለት ነው። ይህንን ለመከላከል የግብር ሥርዓትን የሚደነግጉ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና አሰራሮች ቢያንስ ከአንድ መንግሥት የምርጫ እድሜ በላይ የሚጸኑ፣ በቀላሉና በአንድ ላይ ለሁሉም ሊዳረሱ በሚችሉበት ቋንቋና ስፍራ (ድረ ገጽ) የሚቀመጡ፣ ሲሻሻሉም ሆነ ሲሻሩ ሰፊ ውይይት የሚደረግባቸውና በአንድም ሆነ በሁለት የመንግሥት አካል ፈቃድ ብቻ የማይቀያየሩ መሆን አለባቸው።

ተጨማሪ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል በአገራችን የመሰረታዊ ልማት አውታሮች የሚባሉት የትራንስፖርት፣ የመኖሪያ ቤት፣ የመንገድ፣ የኤሌክትሪክ፣ የውሃ፣ የጤና እና የትምህርት አቅርቦቶች በሙሉ እጥረት ያለባት አገር ነች። እነዚህን መሰረታዊ ልማቶች በመንግሥት አቅም ብቻ በአሁኑ ግዜ በአገራችን እንደሚኖር በሚገመተው 107 ሚልዮን ሕዝብ ማዳረስ አልተቻለም። ስለዚህ የግል ዘርፉ ወይም ነጋዴው በእነዚህ ዘርፎች እንዲሰማራ መበረታት አለበት ። በእነዚህ ለሁሉም መዳረስ ባልቻሉ ዘርፎች የሚሰማራውን መካከለኛም ሆነ ከፍተኛ ባለሃብት በከፍተኛ ግብር ማራቅ ወይም ማስበርገግ የአገራችንን ግብር ሥርዓት ዓላማ አጠያያቂ ያደርገዋል።

> ‹‹ የግብር ሥርዓትን የሚደነግጉ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችናአሰራሮችቢያንስከአንድመንግሥት የምርጫ እድሜ በላይ የሚጸኑ፣ በቀላሉና በአንድ ላይ ለሁሉም ሊዳረሱ በሚችሉበት ቋንቋና ስፍራ (ድረ ገጽ) የሚቀመጡ፣ ሲሻሻሉም ሆነ ሲሻሩ ሰፊ ውይይት የሚደረግባቸውና በአንድም ሆነ በሁለት የመንግሥት አካል ፈቃድ ብቻ የማይቀያየሩ መሆን አለባቸው››

እንዲሁም የአንድ አገር ኢኮኖሚያዊም ሆነ ማኅበራዊ ራዕይ አገር በቀል ቴክኖሎጂና ክህሎቶችን ማዳበር፣ ወደ እውቀት መር ሥርዓትና አስተዳደር መሸጋገር፣ ጤነኛ እና በፖለቲካውም ሆነ በማኅበረሰባዊ ኑሮው ላይ

አዎንታዊ ተጽዕኖ ያለው ማኅበረሰብ መፍጠር፣ ለኢኮኖሚው ሸክም ሳይሆን እንደውም በኢኮኖሚው ላይ እድገት የሚያመጣ ወጣት ማኅበረሰብ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ይህንን ለማድረግ የሚያስችለውንና የግብር ክፍያ ሸክሙን ራዕዩን በሚያንጸባርቅ የግብር ሥርዓት ዓላማ ይቀርጻል። ለምሳሌ እውቀት አመንጪ የሚባሉትን የከፍተኛ ተቋማት፣ የምርምር ማዕከላትን፣ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን፣ የምክር አገልግሎት፣ ከወረቀትና መጽሐፍ እስከ ኮምፒዩተር ያሉ የት/ትና የእውቀት መሳሪያዎችን ሕትመትና የሚድያ አገልግሎት ሰጪዎች ላይ ያለውን የግብር ሸክም በመቀነስ በአንጻሩ በከፍተኛ ትምህርት በማይጠይቁ የሰው ኃይል በሚጠቀሙ እንደ መኪና መገጣጠሚያ፣ ልብስና የመሳሰሉት ፋብሪካዎች ላይ ከፍ ያለ ግብር ሊጥል ይችላል። የተዛባ የግብር ሥርዓት አስቀምጦ በንባብ ልምድና በእውቀት የጫጨ ትውልድ እያሉ ማብጠልጠል አያስኬድም። በጤናውም ዘርፍ እንዲሁ የጤና አቅርቦትን በሚያስፋፉ ባለሃብቶች ላይ በቦታ፣ በአቅርቦት አይነትና ብዛት ላይ የተመሰረተ የግብር ማባበያና ማበረታቻ ሊያስቀምጥ ይችላል።

በሌላው ዓለም ግብር ዋናው የምርጫ ወቅት ቅስቀሳና ውይይት ነጥብ የሚሆነው ግብር ከአገር ራዕይና አካሄድ ጋር በጥብቅ የተሳሰረ ስለሆነ ነው። የግራ እና የቀኝ ክንፍ ፖለቲካ ወይም የማዕከል ፖለቲካ አራማጆች እየተባለ የአንድ ፓርቲ የፖለቲካ አካሄድ ከሚገመገምባበቸው መንገዶች አንዱም ፓርቲው በአገሩ ግብር ሥርዓት ላይ የሚኖረው እይታ ነው። በአገራችን ግን በሕገ መንግሥቱ ከተደነገጉና ግብርን ከሚመለከቱ አንቀጾች ባሻገር በአገራችን የተዘረጋውን የግብር ሥርዓት ለመረዳት የሚያስችል መረጃ ማግኘት እንኳን ለሕዝብ ለግብር ባለሞያውም አዳጋች ነው። ሌላው ቀርቶ የአገራችንን ግብር ሕግጋትና ደንቦች እንዲሁም በየጊዜው የተጠጋገኑበትን ማሻሻያዎች በአንድ ጥራዝ ማግኘት አይቻልም። ስለዚህ ግብር ከፋዩ ለመክፈል በሚሄድበት ወቅት በአንድ ቀን አዳር በአንድ ሰው ፊርማ እንዲከፍል የሚገደደው አዲስ የግብር አይነት ወይም መጠን ሲያጋጥመው ማግኘት በጣም የተለመደ ነው። በዚህ ጭፍን አሰራር ምክንያት የሚጠቀሙ የመንግሥትና የግል ሙሰኞች በርካታ የሕዝብ ገንዘብ አባክነዋል።

ኢዜማ የአገራችን የግብር ሥርዓት ዓላማ የኢኮኖሚያችንን የውስብስበነትና የምርታማነት ደረጃ ያገናዘበ፣ የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ከግምት ውስጥ ያስገባና አገራችን ከሌሎች ምንጮች የምታገኘውን ገቢ ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት ብሎ ያምናል። ስለዚህ አሁንም ኢዜማ ደግሞ የሚመክረውና የሚያምንበት ቀዳሚ ተግባር የግብር ግልጽነት ነው። የግብር ሕግጋትን የተመለከቱ መረጃዎች ግልጽነትና ተደራሽነት ከግብር ክፍያ መረጃ እኩል በፍጥነት መተግበር ያለበት ሥራ ነው። በቅድሚያ ግብርን መደንገግ የአንድ ፓርቲ፣ የአንድ አስፈጻሚና ሕግ አውጪ አካል ብቻ ሥልጣን የሚያደርገውን አሰራር በማሻሻል ተጨማሪ ባለድርሻ አካላት በሂደቱ ውስጥ በሙሉ እንዲሳተፉ የሚያስችላቸውን አሰራር በዘላቂ ሕግ ያስቀምጣል። በረጅም ግዜ እቅድም ይህ አሳታፊ አሰራር ሕገ መንግሥታዊ ሽፋን እንዲያገኝም የተቻለውን ጥረት ያደርጋል።

## 3)የግብርሥርዓት ርቱዕነት

የአንድን አገር የግብር ሥርዓት ለመፈተሽ በዝርዝርም ሆነ በርዕዮተ ዓለም/ፍልስፍና ብዙ መስፈርቶች ቢኖሩም ለዚህ ጽሑፍ ሲባል በሁለት መመርመሪያ ነጥቦች እናጠቃልላቸዋለን። ሚዛናዊነት የመጀመሪያው ሲሆን ይህም የግብር መክፈል ሸክሙን አጋዳይነት ወይም መመጣጠንን ይመለከታል። ግብር አንዱ የከፋዩን አካል ጎድቶ ሌላውን ከጠቀመ የተዛባና አገራዊ ቀውስ የሚያስከትል ይሆናል። ሕዝባዊነት ደግሞ የግብር ሥርዓቱ የቆመው ለአገሩ ዜጋ መሆን አለመሆኑንና የብዙኃኑን ክፍል የኑሮ ደረጃ የሚያሻሽል እንጂ የሚያባብስ አለመሆኑን ይፈትሻል።

### ሀ) ሚዛናዊነት

ከላይ በክፍል አንድና ሁለት ከዘረዘርናቸው ጉዳዮች በተጨማሪ ግብርን ከማኅበራዊ ፍትሕ ጋር የሚያዛምደው ሶስተኛው ነጥብ ከላይ በመጠኑ ያነሳነው የግብር ሸክም ወይም ሚዛን ጉዳይ ነው። ከመንግሥት ሰራተኛ ውጪ ያለው ግብር ከፋይ የግል ዘርፉ ነው። የግል ዘርፉ የሚባለው ደግሞ በምርትና በአገልግሎት ሰጪነት የተሰማራው ነጋዴ ወይም ባለሃብት በሙሉ ነው። ይህ የግል ዘርፍ የውጪውንም የአገር ውስጡንም ከመንግሥት ድጋፍ የሚያገኘውንም የማያገኘውንም፣ አነስተኛውንም በጣም ከፍተኛውንም ያካትታል። መንግሥት እራሱ የሚሳተፍባቸውንና እንደ አየር ትራንስፖርት፣ ኤሌክትሪክ፣ ቴሌኮሙኒኬሽን እና ውሃ አቅርቦት ያሉ ዘርፎችንም ያካትታል።

ከዚህ ቀደም ኢዜማ በተደጋጋሚ እንዳሳወቀው አሁን አገራችን ባለችበት የምጣኔ ሃብት አነስተኛ ደረጃና የመሰረታዊ ልማት አገልግሎቶች ዝቅተኛ አቅርቦት ደረጃ ሙሉ በሙሉ ልቅ የሆነ ኢኮኖሚ ፍልስፍናም ሆነ አሰራር መከተል አንችልም። የብዙኃኑ ኑሮ ከእጅ ወደ አፍ በሆነበትና በኑሮ ውድነት በሚማመረርበት በአሁኑ ሰዓት ልቅ ኢኮኖሚ መከተል የመሰረታዊ ልማት አቅርቦቶች ላይ የሚያደርሰውን የዋጋ ጭማሪና ሌሎች አሉታዊ ተፅዕኖዎች መቋቋም አይችልም። የመንግሥትን ሚና ከመሰረታዊ ልማት አቅርቦቶች ከሚገባው በላይና ያለ በቂ ጥናት መቀነስ አገራችንን ዛሬ ሞዛምቢክ፣ ዛምቢያ እና ዚምባቄ የሚዋዥቁበትን አስደንጋጭና በ21ኛው ክፍለ ዘመን ሊታሰብ በማይችል የጋርዮሽ ዘመን መቀመቅ ከማውረድ በስተቀር ሌላ አስተዋጾ አይኖረውም።

እርግጥ ባለፉት 28 ዓመታት የተከተልነው የተዛባ የ"ልማታዊ መንግሥት" አረዳድና ሥርዓት መንግሥትን ብሎም በሥልጣን የቆየውን ፓርቲ እስከ እንጀራ ችርቻሮ ድረስ በየዘርፉ እንዲሰማራ እና በግል ዘርፉ ላይ ኢፍትሐዊ ውድድር፣ የገንዘብና የውጭ ምንዛሪ ሽምያ በተለይም የግብር ሸክም መዛባት አስከትሏል። ስለዚህ የግብር ሥርዓትን ከማሻሻልና ፍትሐዊ ከማድረግ ጎን ለጎን መንግሥት በንግድ ሥርዓቱ ላይ ያለው ሚና ጉዳይ መነሳቱ አይቀርም። ሁለቱንም ጉዳዮች በአንድነትና በእኩልነት/በሁለገባዊ መንገድ ለመገምገም ለማስቻል አሁን ያለውን ከፍተኛ የመረጃ እና የጥናት ክፍተት መድፈን፣ አገራዊ እና እውቀት መር ተሳትፎ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ግልጽ ነው።

ይሁንና ለጊዜው ባለው የመረጃ እና የጥናት ደረጃ እንኳን የአገራችንን የግብር ሥርዓት በተመለከተ በሰፊው የሚታወቁና የምንኖራቸው የተወሰኑ በእውነታ የተደገፉ ትዝብቶችን ማንሳት ይቻላል።

- አገራችን ፌደራላዊ አስተዳደር በመከተሏ የተነሳ ታገኛዋለች ተብሎ ይጠበቅ ከነበረው ጠቀሜታ አንዱ

በክልሎች መካከል ፍትሐዊ የግብርና የሃብት ስብጥር ይኖራል የሚል ነበር፡ ፡ ቢሆንም ከ25 ዓመታት በኋላ አሁንም የአገሪቱ ከፍተኛ ግብር ከፋይ ዋና ከተማዋ አዲስ አበባ ነች፣ ከፍተኛ ግብር ሰብሳቢው የመንግሥት አካልም ፌደራል መንግሥቱ ነው።

- ልማታዊ መንግሥት የተባለው አሰራር የግል ሴክተሩ አቅም እስኪጎለብት ድረስ የሚቆይና የግል ሴክተሩ የገንዘብ አቅም ሊሸፍናቸው በማይችላቸው ዘርፎች የመንግሥት አካላትን የሚያሰማራ እንደሆነ ቢነገርም አሁንም ከፍተኛው የግብር ከፋይ የግል ዘርፉ ነው።
- ከግል ዘርፉም ከፍተኛው የግብር ከፋይ ዘርፍ እንደ ሆቴል፣ ባርና ካፌ፣ ባንክና ፋይናንስ እና የመሳሰሉትን የሚያካትተው የአገልግሎት ዘርፉ ነው። (በ2010 ዓም የገቢዎች ባለሥልጣን መረጃ መሰረት 60% የሚደርስ) አምራች ወይም እሴት ጨማሪው (ግብርና እና ኢንዱስትሪ) ዘርፍ አይደለም።
- ከፍተኛ ግብር ከፋይ ይሆናሉ ተብለው ሲጠበቁ የነበሩትና ከ90% በላይ በውጭ ኢንቨስተር እጅ ላሉ የንግድ ዘርፎች ከተሰጣቸው የማበረታቻ ጥቅማ ጥቅም ተለጣጭነት የተነሳ የሚከፍሉት ግብር አሁንም አነስተኛ ብሎም ወደ ዜሮ የሚጠጋ ነው።
- በአንጻሩ አዳዲስ የግብር አይነቶች እንደ ተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) ወይም የግብር ጭማሪዎች (የገቢ ግብር/ኢንካም ታክስ ወደ 30% ማደግ) በአሰራርና በአቀራረጽ መዛባት የሕዝቡ ኑሮ እና ኢኮኖሚው ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ አስከትለዋል። (ለምሳሌ የደሞዝ ሰራተኛውም፣ ሀኪሙም፣ የቢራ ፋብሪካ ባለቤቱም፣ የምክር አገልግሎት ሰጪው ወይም ኮንሳልታንቱም እኩል 30% የገቢ ግብር የሚከፍሉበት አሰራር መሰረታዊ ኢፍትሐዊነት፣ ቫት አገር በቀል በሆኑና የቅንጦት ባልሆኑ ምርቶች ላይ አይውልም ቢባልም በግብር ሰብሳቢ ደካማ አሰራር ምክንያት ድንገት ያስከተለው የኑሮ መወደድ እስካሁን አለመታረሙ ወዘተ)
- በከፍተኛ ግብር ከፋይ በሆኑት አካባቢዎች እንኳን የመሰረታዊ ልማት አቅርቦቱ መቀነስና ከዓመት ዓመት የኑሮ ውድነትና የሕዝብ ቁጥር እየጨመረ በአንፃሩ የአገራችን ምርቶች በአይነትም ሆነ በብዛት ከፍተኛ የሚባል ለውጥ ሳያሳዩ በየዓመቱ መንግሥት ሰበሰብኩት የሚለው የግብር መጠን መጨመር ለመቀበል ያዳግታል፡፡ አልያም ተሰበሰበ ተብሎ የሚነገረው የግብር መጠን እውነት ከሆነ በተመሳሳይ የግብር ከፋዩ ላይ ከዓመት ዓመት የግብር ጭማሪ መደረጉን የሚያሳይ ነው የሚሆነው፡፡

## ለ) ሕዝባዊነት

ለእነዚህና በርካታ እዚህ መዘርዘር ለማንችላቸው ሁኔታዎች ያበቃን ዋናው ምክንያት ሕዝብንና አገርን የሚቀርጽ ሳይሆን የጥቂቶችን የግል ጥቅም የሚያመቻች የግብር ሥርዓት ነው። የአገራችን ኢኮኖሚ እድገት የሚመጣው በመንግሥት እና በውጪ ኃይሎች አማካኝነት እንጂ በአገር በቀል የግል ዘርፉ ኃይል አይደለም የሚል ፍጹም የተሳሳተ አመለካከት አገር በቀሉን የግል ዘርፍ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ዜጋነት ለዳረገ ከፍተኛ የግብር እና ተያያዥ ማበረታቻዎች መድሎ/አድሎ (Discrimination) አምጥቷል።

ከግብርና መር ወደ ኢንደስትሪ መር ኢኮኖሚያዊ እድገት የተደረገውና በጥናት ያልተደገፈ ቀኝ አዞር ለውጥና የተከተለው የግብርና "ማበረታቻ" በግብርና የሚተዳደረውን ብዙኃኑን ወደ ተሻለ ኑሮ ደረጃ ብድግ ከማድረግ ይልቅ መሬታቸውን፣ ላባቸውንና፣ ልጆቻቸውን ለጥቂት ባለሃብቶች ወደ ባርነት ለሚጠጋ ኑሮ ዳርጓል። የአገራችንን ኢኮኖሚ ኤክስትራክቲቭ (extractive)/"ደም መጣጭ" ወይም እንደ ማዕድን ቁፋሮ ሁሉ ከብዙኃኑ ነጥቆ ወደ ጥቂቶች እጅ የሚጠቀልል ኢኮኖሚ ነው ከሚባልባቸው አንዱ ምክንያት ይህ ነው። (ሌሎቹ ምክንያቶች ለምሳሌ የመሬት ፖሊሲው፣ የመኖሪያ ቤት ፖሊሲው የጤና እና የትምህርት ፖሊሲው ናቸው) በተሳሳተ እይታ በ"ማኑፋክቸሪንግ"ና በኢንዱስትሪ ላይ የተንጠላጠለ የእድገት ተስፋ በበኩሉ ባስከተለው የኢምፖርት ዲፔንደንሲ አገር በቀል አምራቾች ከደረሰባቸው ጉዳት በተጨማሪ እነሱን በርካታ ማበረታቻዎች ከተሰጣቸው የመንግሥት እና የውጭ ንግዶች እኩል የሚቀጣ የግብር ሥርዓት በርካታውን አምራች ከአምራችነት ወደ አገልግሎት ሴክተሩ ያባረረ ብሎም ከንግድ ውጪ ያደረገ ሥርዓት ነው።

በተለይ ደግሞ የመንግሥት የግብር ሥርዓት አስፈጻሚ አካላት የሰው፣ የገንዘብና የቴክኖሎጂ አቅም ሳይጎለብት ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ የተፈቀደላቸው የኢንቨስትመንት አይነቶች እና ብዛት የገንዘብና የሰው ኃይል አቅም ውስብስብነት አገራችን የሚገባትን የግብር መጠን በሕገ ወጥ መንገድ እንድታጣ አድርጓታል። (ለምሳሌ ባለፉት 10 ዓመታት ብቻ 32 ቢልየን ዶላር እንዳጣን ጥናቶች ያመለክታሉ፣ ይህ ቁጥር የግምት ውጤት ከመሆኑም ባሻገር በሙሰኝነትና በጥቁር የገንዘብ ምንዛሪ ገበያ የሚወጣውንም ገንዘብ የሚያካትት ነው። ስለዚህ በግብር ማምለጥ/ሽወዳ የሚወጣውን ገንዘብ ለማጥናት ከላይ የመከርነውን የግብር መረጃ መረብ በመዘርጋት የከፍተኛ ግብር ከፋዩን ቁጥር ከሌላው እንዲሁም በውጭ አገር የተያዙትን የንግድ ዘርፎች ከአገር ውስጦቹ መጀመሪያ በቅጡ መለየት ያስፈልጋል።)

በአሁኑ ግዜ አገራችንን ጨምሮ በርካታ የአፍሪካ አገራት ዋነኛ ችግር የመልቲናሽናሎች ከፍተኛና ረቂቅ የፋይናንስ አሰራሮችን ባለመረዳት የተነሳ የሚመጣ የግብር ሽወዳ ነው። እነዚህ ድርጅቶች ከሚጠቀሙባቸው አሰራሮች አንዱ ስምምነት ሽመታ ወይም (treaty shopping) ይባላል። ይህም ማለት ድርጅቶቹ አገራችን ከተለያዩ የውጭ አገራት ጋር የተፈራረመቻቸውን ገንዘብ/ግብር ነክ ስምምነቶች በአትኩሮት በማጥናት አገራችን የጣለቻቸውን እያንዳንዳቸውን የግብር አይነቶች ለማምለጥ የሚያስችላቸውን የሕግ ክፍተቶች በሙሉ መጠቀም ማለት ነው። ለምሳሌ የገቢ ግብርን እንዲያስከፍላቸው የሚያስገድዳቸውን ሕግን በማበረታቻ በመሻር ለ10 ዓመታት የሚቆይ የግብር እረፍት (Tax Holiday) ካለ ድርጅቱ 10 ዓመት ሲሞላው ኪሳራ አስመዝግቦ መልሰው በአዲስ ስም እንደ አዲስ ኢንቨስትመንት ያስመዘግቡታል። ወይም ደግሞ የገቢ ግብርን ለመቀነስ ወጪያቸውን በተጋነነመልኩ ለመጨመር የሚያስችላቸውንና በአስፈጻሚው አካል አቅም ውስንነት ክትትል ሊደረግባቸው በማይቻልባቸው አገራት ወጪ እንደተደረገ አድርጎ ያስመዘግባሉ። ለምሳሌ አንድ ቢራ ፋብሪካ ለበጀት ክትትል ሥርዓት ክትትል የሚረዳ ሶፍትዌርና ማኔጅመንት ሆላንድ ውስጥ እንደዚህ ለሚባል ድርጅት በየዓመቱ 3 ሚልየን ዩሮ እከፍላለሁ፣ ክፍያው

ገቢ የተደረገውም በሞሪሽየስ ነው ቢል ምንም እንኳን ተዓማኒ ባይመስልም የወጪውን እውነትነት የሚረጋገጥበት ሕግም ሆነ አሰራር አልተቀመጠም፡፡

በተመሳሳይ የግብር ሥርዓቱና ሰብሳቢው አቅም ውሱንነቱ እንደ ድለላ፣ ጉዳይ ፈጻሚነት፣ አየር በአየር ንግድና እና ጥቁር ብዙኃኑን ከማደህየትም ባሻገር ለሰራተኞች ሰብዓዊ መብት ጥሰት፣ ለተፈጥሮ ሃብት መመናመን፣ ለኢፍትሐዊ የመሬት ቅርምት እንዲሁም ለመኖሪያቤትና ለሌሎች መሰረታዊ ልማት አቅርቦቶች እጥረት መባባስ ምክንያት ነው፡፡

በአጭሩ በዚህ አሰራርና ባልተጠናከረ

## ‹‹ ኢዜማ በዚህ ረገድ የሚደረጉ ማሻሻያዎችን ይከታተላል፣ በባለሞያ ያስጠናል፡፡ አገራችን በአሁኑ ወቅት የምትሰበስባቸው የግብር አይነቶች፣ መጠን እና በተለያዩ የአገራችን እና የመንግሥት አካላት መካከል ያለውን የግብር ክፍፍል ፍትሐዊነት በተመለከተ በወደፊት የዝርዝር ፖሊሲ አቅጣጫዎች የሚቀመጡ ይሆናሉ፡፡››

የምንዛሬ ገበያ በግብር ሥርዓቱ ያልተካተቱ ወይም የከርሰ ምድር የንግድ እንቅስቃሴ (underground economy) ተብለው የሚጠሩ የኢኮኖሚ ዘርፍ አይነቶች እንዲስፋፉ አድርጓል፡፡ (በዚህ መንገድ አገራችን የምታጣው ገቢ ከአገር ውስጥ ባይወጣም እንኳን በአገር ውስጥ የሚንቀሳቀሰውን የገንዘብ ግብይት በማዛባትና የካሽ ግባዓቱን በመጨመር ለዋጋ ግሽበት፣ እንደ መሳሪያና የሰው ዝውውር ላሉ ተያያዥ ሕገ ወጥ ንግዶች ያጋልጣሉ)

### ማጠቃለያ

እነዚህና ሌሎች በርካታ በእለት ተእለት ኑሯችን በተጨባጭ የሚታዩ ምልክቶች ተደማምረው ነው የአገራችን የግብር ሥርዓት ለአገሩ ዜጋ የማያዳላ እና የብዙኃኑን ሃብት የሚቀማ/በድኃው ብዙኃን ጫንቃ ላይ የቆመ ነው ለማለት የሚያስደፍረን፡፡ ይህ ሚዛኑ ያጋደለ የግብር ሥርዓት አገራችን ስትከተለው የቆየችውን የተዛባ የኢኮኖሚ ፖሊሲና ዲሞክራሲያዊ ያልሆነ የፖለቲካ ሥርዓት ውጤት ነው፡፡ ኢፍትሐዊ የግብር ሥርዓት የሚያመጣው የኢንቨስትመንት አይነት የግብር ሰብሳቢ ኃይል የእውቀት፣ የክህሎትና የቴክኖሎጂ አቅም ላይ የሚደረግ ማንኛውም የንግድ፣ ኢንቨስትመንትና የኢኮኖሚ ፖሊሲ ማሻሻያ አልፎ ተርፎም በመንግሥት የተያዙ የመሰረታዊ ልማት አውታሮችን ያለ በቂ ሁለገብ ጥናት፣ ያለ አሳታፊ ውይይት በፍጥነት ማሻሻል ሕዝባችንን ለተጨማሪ ችግር ይዳርገዋል፡፡ የግብር ሥርዓቱ ያሉትንም ኢንቨስተሮች በአግባቡ መቆጣጠር እና ተገቢውን ገቢ ማስገኘት አላስቻለም፡፡ ከዓመት ዓመት ለግብር ከፋዩ በሰቆቃ ለሰብሳቢው በዛቻ እና በታላቅ ድል አድራጊነት መሰብሰቡ የሚነገረው ግብር የሚሰበሰበውና የግብር ሥርዓቱ የመሰብሰብ አቅም የሚፈቅደው/የተቀረጸው አሁንም ለአገር ውስጡ ግብር ከፋይ ነው፡፡

ኢዜማ በዚህ ረገድ የሚደረጉ ማሻሻያዎችን ይከታተላል፣ በባለሞያ ያስጠናል፡፡ አገራችን በአሁኑ ወቅት የምትሰበስባቸው የግብር አይነቶች፣ መጠን እና በተለያዩ የአገራችን እና የመንግሥት አካላት መካከል ያለውን የግብር ክፍፍል ፍትሐዊነት በተመለከተ በወደፊት የዝርዝር ፖሊሲ አቅጣጫዎች የሚቀመጡ ይሆናሉ፡፡ ለምሳሌ የገቢ ግብር በጅምላ ለሁሉም አንድ መጠን (Fixed Amount) የመሆኑ፣ ክልሎች መሰብሰብ የሚችሉት የግብር ጣራ መጠን መሻሻል ማስፈለጉ፣ ከዚህ ጋር ተያይዞ በፌደራሉና በክልል መንግሥታት መካከል ያለው የሃብት ክፍፍል ሥርዓት መሻሻል ማስፈለጉ፣ አገራችን የተፈራረመቻቸውን ገንዘብ ነክ ስምምነቶች ከኢንቨስትመንት እና ከንግድ ሕግጋት አንጻር መፈተሽ ማስፈለጉ፣ ለውጭ ኢንቨስተሮችና ባለሃብቶች የሚሰጡ ጥቅማ ጥቅሞች ከግብር ሥርዓቱ ጋር ተጣጥመው መሄድ እንዳለባቸው እንዲሁም የገቢ ግብር መጠን ወለል (Non Taxable Income) አሁን ካለው ከፍ ማድረግ እንዳለበት እንዲሁም እንደ ድለላና የገንዘብ ግብይቶች ያሉ አዳዲስ የንግድ ዘርፎችን በግብር ሥርዓቱ ውስጥ መካተት እንዳለባቸው እናምናለን፡፡

ይሁንና ዝርዝር ጉዳዮች ውስጥ እና ለብዙኃኑ የማይጠቅም የግብር ርዕዮተ ዓለም ክርክር ከመግባት ይልቅ ሕዝባችን በቀላሉ ተረድቶ በዕለት ተዕለት ሕይወቱ ውስጥ በተጨባጭ የሚያያቸውን ምሳሌዎች በማንሳት ለአገራችን የግብር ሥርዓት የጋራ ራዕይ ማበጀት ይቀድማል ባይ ነን፡፡ የጋራ የግብር ሥርዓት ራዕይ ስንል ዜግነትን ማዕከል በማድረግ የአገራችንን የግል ዘርፍ የሚያበረታታ ማለታችን ነው፡፡ አገራዊ የግብር ሥርዓት ስንል የሕዝቡን ተጨባጭ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ የሚያንጸባርቅ ማለታችን ነው፡፡ ብዙኃን የሚስማሙበት የግብር ሥርዓት ዓላማ ስንል ለአገራችን የምንመኘውን መልካም ማኅበረሰብ መቅረጽ የሚያስችለንና የሚበረታታውን የሚያበረታታ አሉታዊ ተጽዕኖው የሚበዛውን የሚከላከል ሥርዓት ማለታችን ነው፡፡

# ኢዜማ፣ ከሚዛን አማን ከተማ ነዋሪዎች ጋር ተወያየ

ሕዳር 18 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ ፓርቲ (ኢዜማ) ያሳለፍነው ቅዳሜ ሕዳር 13 ቀን 2012 ዓ.ም በሚዛን አማን ከተማ ቤንች ሸኮ ዞን የተሳካ ሕዝባዊ ስብሰባ ማካሄዱን የኢዜማ ዋና ፀሐፊ አበበ አካሉ ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡ በሕዝባዊ ስብሰባው ላይ ቁጥራቸው ከ700 እስከ 800 የሚደርሱ የአካባቢው ነዋሪዎች መሳተፋቸውን የገለፁት ዋና ፀሐፊው፣ በስብሰባው ላይ የኢዜማ ፕሮግራምና ደንብ ምን እንደሚመስል ለስብሰባው ተሳታፊ ገለፃ እንደተደረገና በወቅታዊ ጉዳዮች ላይም ከአካባቢው ነዋሪዎች ጋር ውይይት መደረጉን አስረድተዋል፡፡ በስብሰባው ላይ ከኢዜማ አባላትና ደጋፊዎች ይልቅ አብዛኛው ተሳታፊ የነበረው የኢዜማ አባል ያልሆነው የሕብረተሰብ ክፍል መሆኑን ፀሐፊው ገልፀዋል፡፡ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 8፡00 በዘለቀው ስብሰባ ላይ የአካባቢው ነዋሪዎች፣ የደኢህዴን አመራሮች፣ የሚዛን ቴፒ መምሕራን እንዲሁም የደቡብ ቴሌቪዥን የተገኙ መሆናቸውን ፀሐፊው ጠቁመዋል፡፡

የስብሰባው ተሳታፊዎች ኢዜማ ምን አይነት የፌደራል አወቃቀር ይከተላል? ሕገመንግስቱ መሻሻል ያለበት ከምርጫ በፊት አይደለም ወይ? ኢዜማ ቢመረጥ የሕግ የበላይነትን እንዴት ያስከብራል? የሚሉ ጥያቄዎችን አንስተዋል፡፡ ከስብሰባው ተሳታፊዎች ለተነሱት ጥያቄዎችም የኢዜማ ዋና ፀሐፊ አበበ አካሉ የሚከተሉትን ምላሾች ሰጥተዋል፡፡

ኢዜማ ምን አይነት የፌደራል አወቃቀር ይከተላል? ለሚለው ጥያቄ የመንግስት አደረጃጀት ፌዴራላዊ እንደሚሆንና የፌዴራል መንግስትና የአካባቢ አስተዳደሮች እንደሚኖሩና የአስተዳደር አካባቢዎች አወቃቀር መልከአ ምድራዊ አቀማመጥን፣ የሕዝብ አሰፋፈር ለአጠቃላይ አስተዳደራዊና ለልማት ሥራዎች አመቺነትን፤ ቋንቋ፤ ባህል ስነልቦናዊ ቁርኝት እና ታሪክን፤ የሃብት ስብጥርና ፍትሃዊነት ለብሔራዊ መግባባት አመቺ ሁኔታ መፍጠርን፤ መሠረት ባደረገ ሁኔታ ይሆናል ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል፡ ፡ ሕገመንግሥቱ መሻሻል አለበት በሚል ለተነሳው ጥያቄም ዋና ፀሐፊው ሲመልሱ "ሕገመንግሥት የማሻሻል ኃላፊነት በምርጫ የተመረጠ መንግስት ድርሻ ሊሆን ይገባል፤ በሕዝብ ድምፅ ያልተመረጠ መንግሥት ባለበት ሁኔታ አሁን ላይ ሕገመንግሥቱን እናሻሽል ማለት መግባባት ላይ የማያደርስ ይሆናል" ብለዋል፡፡ የሕግ የበላይነት ጉዳይም ኢዜማ ከምንም በላይ የሚያሳስበውና አፅንኦት የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑንና ሰላምንም ሆነ የሕግ የበላይነት ለማስከበር ኢዜማ ቁርጠኝነት እንዳለው ገልፀዋል፡፡

ወቅታዊ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ጉዳይ በሚመለከት በተደረገው ውይይት ላይም ነዋሪዎች መንግሥት የሕግ የበላይነትን እያስከበረ ባለመሆኑ በየጊዜው የዘር ግጭቶች እየተነሱ የዜጎች ሕይወት እየተቀጠፈ እንዳለ አስረድተዋል፡፡ "የፀጥታ ጉዳይ እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል፤ ወጥተን መግባት አልቻልንም ሲሉም" ነዋሪዎች ሀሳባቸውን ሰንዝረዋል፡፡ በተጨማሪም በሚዛን አማን የመሰረተ ልማት አለመሟላት እንዲሁም በግንባታ ላይ ያሉ መሰረተ ልማቶችም በመጓተታቸው ነዋሪው ለችግር እንደተዳረገ በስብበሳው ላይ ተገልጿል፡፡ ነዋሪዎች ለአብነትም በሚዛን አማን ከተማ ይገነባል ተብሎ እስካሁን ግንባታው ያልተካሄደው የሚዛን አማን አውሮፕላን ማረፊያ ጣቢያን አንስተዋል፡፡

የኢዜማ ዋና ፀሐፊ አበበ አካሉ ከሚዛን አማን ከተማ ነዋሪዎች ጋር ባደረጉት ሕዝባዊ ውይይት በእጅጉ መርካታቸውን ገልፀው ለስብሰባው መሳካት ጥሩ ትብብር አድርገውልናል ያሉትን የከተማው አስተዳደር አመስግነዋል፡፡

# ከሠራተኛ እና ከሙያ ማኅበራት ጋር መቀራረብ አስፈላጊ እንደሆነ ተገለፀ

ሕዳር 18 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ቅዳሜ ኅዳር 13 ቀን 2012 ዓ•ም የኢዜማ ፕሮግራሞችና የሙያ ማኅበራት ሚና በሚል ርዕስ ከተለያዩ የሙያ ማኅበራት አመራሮች፣ አባላትና መምህራን ጋር በሰሜን ሆቴል ውይይት አካሄደ፡፡

በውይይቱ መክፈቻ ላይ የኢዜማ ሙያ ማኅበራት ተጠሪ እሌኒ ነጋሽ ኢዜማ፣ የሙያ ማኅበራት የሚጠበቅባቸውን ማኅበራዊ ኃላፊነት መወጣት እንዲችሉ ለማገዝ በቁርጠኝነት ሥራ እየሠራ እንደሚገኝ አስረድተዋል ፡፡ የኢዜማ መሪ ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) ስለ ሠራተኛ ማኅበራት ከዓለም ዓለም አቀፍ አደረጃጀት፣ ተሞክሮና አሠራር እንዲሁም በኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም የነበረው የማኅበራት አደረጃጀትና ተግዳሮቶችን የሚመለከት ጽሑፍ ያቀረቡ ሲሆን የተረጋጋ እና ማኅበራዊ ፍትህ የሰፈነበት የፖለቲካ ሥርዓት ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲመሠረት የሙያ ማኅበራት ምን አይነት ሚና ሊጫወቱ ይገባል በሚለው ነጥብ ላይ ውይይት ተደርጓል። ብርሃኑ «ከሠራተኛ እና ሙያ ማኅበራት ጋር ውይይት ማድረግና መቀራረብ አለብን፡፡ ይህን የምንለው ኢዜማን ይጠቅማል ከሚል ሀሳብ ብቻ ሳይሆን ሙያ ማኅበራት ለሀገር እድገት አስፈላጊ ስለሆኑ እና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ያለ ሙያ ማኅበራት ስለማይመጣ፤ የማኅበራት መዳከም የዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ስለሚያዳክመውም ጭምር ነው፡፡» ብለዋል፡፡

ከውይይቱ በኋላ እሌኒ ነጋሽ የኢዜማና የሙያ ማኅበራት ግንኙነት ላይ ትኩረቱን በማድረግ የተዘጋጀው የመወያያ መድረክ የኢዜማን ፕሮግራም በማስተዋወቅና




ግልጽ በማድረግ ማኅበራት ያለባቸውን ክፍተቶች እንዲሁም ማኅበራት ከኢዜማ ምን እንደሚፈልጉ ከተወያዮቹ ግብዓት መሰብሰቡን ገልፀዋል። በተጨማሪም፣ የማኅበራት የመደራጀት ነጻነት፣ ማኅበራት ላይ ያለው የህግ ማዕቀፍና አዋጅ መልሶ መፈተሽ እንዲሁም በቅጥር ኤጀንሲዎች የሚካሄደው የሰዎች ጉልበት ብዝበዛን እንዴት ማስቀረት እንደሚቻል ግብዓት ማግኘታቸውን አስረድተዋል፡፡